# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

ሐምሌ ፲፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም

## ኢትዮጵያ ለግፍ ሥርዓትና ለፖለቲካና የኅሊና እስረኞች ማጎሪያ ቦታ አይኖራትም!

ላለፈው አንድ ዓመት ከስምንት ወር በሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባገነን ቡድን በእስር ሲሰቃዩ የቆዩ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ መሪዎችና አባላት÷ እንዲሁም የነፃው ፕሬስና የሲቪክ ማኅበረሰብ አባላት ዛሬ ዐርብ ሐምሌ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም ከእስር ተለቀዋል፡፡ እነዚህ የኅሊና እስረኞች ከእስር በመፈታታቸው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የተሰማውን ልባዊ ደስታ እየገለጸ÷ በእስር ሲሰቃዩ ለቆዩት ወገኖች እንዲሁም ለቤሰቦቻቸውና ለወዳጆቻቸው እንኳን ደስ ያላችሁ ይላል፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት በአነ አቶ መለስ መመሪያ የዕድሜ ልክ እስራት ተበይኖባቸው የነበሩት ወገኖች በዛሬው ቀን ከእስር መፈታታቸው ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያስደሰተ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ወደ እስር ቤት ተወርውረው ላለፉት ሁለት ዓመታት በእስር ሲንገላቱና ሲሰቃዩ የነበሩት ወገኖች የታሠሩት ወንጀል በመፈጸማቸው ሳይሆን በአሸባሪው አምባገነን አገዛዝ የትዕቢትና የማን አለብኝነት ትእዛዝ ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው፡፡ የሕዝብን ድምፅ የሰረቁት÷ በየአደባባዩ የጅምላ ርሸናዎችን ያካሄዱት÷ በየእስር ቤቱ ሕዝብን ያሰቃዩት ለፍርድ ቀርበው ለጥፋታቸው ውሳኔ ሳይሰጥ÷ መብትን ተጠቅሞ ሰላማዊ ተቃውሞ ማሰማት ይህን ያህል ጊዜ ለእስር መዳረጉ የሚወገዝ ተግባር ቢሆንም የአምባገነኖች ባህሪ ስለሆነ የሚያስገርም አይደለም፡፡

የነገዋ ኢትዮጵያ ለአምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓቶች አዙሪትና እነሱ ለቀፈቀፏቸው የፖለቲካና የኅሊና እስረኞች እስር ቤቶች ቦታ ሊኖራት አይገባም፡፡ በዛሬው ዕለት እነዚህ ወገኖቻችን ከእስር የተለቀቁት በሕዝባችን ያልተቋረጠ ትግልና ጥረት ነው፡፡ እነኝህ የኅሊና እስረኞች መለቀቃቸው ከልብ ሲያስደስተን÷ አስተማማኝ ሰላምና ዘለቄታዊ ደስታ ሊገኝ የሚችለው አምባገነን አገዛዝ ተወግዶ ሕዝባችን መብቱ ሲጠበቅና ሲረጋገጥ÷ ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ከእስር ተፈትተው የነፃነት እስትንፋስ ሲተነፍሱና ልዩነቶችን በሰከነ ሁኔታ ለመፍታትና ተከባብሮና ተቻችሎ በእኩልነት ለመኖር እንዲቻል ሥርዓት ያለው አገር-አቀፍ እርቅና ሰላም ሲኖር ብቻ ስለሆነ ይህ ሁኔታ እውን እንዲሆን አገር ወዳድና ዴሞክራቶች ሁሉ ሕዝባዊ ትግሉን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

ሕዝባዊ ትግል ለአስተማማኝ ዘለቄታዊ ሰላም!
የተባባረ ትግል ለአስተማማኝ ድል!!

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132